በሕግ አማካይነት ለአካል ጉዳተኞች እኩል የሥራ ስምሪት ዕድሎችን ማስከበር

የትምህርትና የሥልጠና መመሪያ

ኮታዎች

4

የመማር ዓላማዎች

- የኮታ ዘዴዎችን እንደ አዎንታዊ ተግባር እርምጃዎች **ማወቅ**።
- ሦስት መሠረታዊ የኮታ ዘዴዎች ዓይነቶችና ተያያዥ ጉዳዮችን **መለየት**።
- የኮታ አሠራር በተግባር እንዲሠራ ለማድረግ ውጤታማ ስትራቴጂዎችን **መንደፍ**፡-
  - የተወሰኑ አካል ጉዳተኞችን ዒላማ ማድረግ፤
  - ወጥ ወይም የተለያየ የኮታ መጠን፤
  - ተገቢው የኮታ መቶኛ እንዴት እንደሚለይ፤
  - የትኛው የአሠሪ መጠን ዒላማ እንደሚሆን።

ሦስት ዓይነት የኮታ ዘዴዎች

- በተጠናከረ ዘዴ የሚደገፍ የኮታ አሠራር (የኮታ ቀረጥ ዘዴ)።
- ውጤታማ ማጠናከሪያ የሌለው አስገዳጅ ኮታ።
- እንደ መንግሥት የውስጥ መመሪያ ባለ መሪ ሃሳብ ላይ የተመሠረተ አስገዳጅ ያልሆነ ኮታ።

የኮታ ቀረጥ ዘዴ

- የተወሰኑ የሥራ መደቦች መቶኛ ከአካል ጉዳተኞች እንዲሰጡ በአሠሪዎች ላይ የተጣለ ግዴታ።
- በሕጉ ተሸፍነው ግዴታቸውን የማያሟሉ አሠሪዎች ሁሉ ማካካሻ እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ (ቀረጥ ወይም መቀጫ ይባላል)።
- የማካካሻ ክፍያዎች የአካል ጉዳተኞችን የሥራ ስምሪት ለመደገፍ ወደ ፈንድ ገቢ ይደረጋል።

የቀረጥ ፈንዶች - ምሳሌዎች

- **በኦስትሪያ** ፈንዱ አሠሪዎች ያለባቸውን ዕዳ በሚያሰላና ይህንን በሚያሳውቃቸው የመንግሥት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ይተዳደራል።

- **በፈረንሳይ** ፈንዱ የአሠሪዎች፣ የሠራተኞችና የመንግሥት ተወካዮችን ባቀፈ (AGEFIPH) በሚባል ድርጅት ይመራል

- **በፖላንድ** ለብሔራዊ ፈንዱ ተከፋይ መሆን ያለባቸውን ግብሮች ግብር ሰብሳቢዎች ለመሰብሰብና ለማከፋፈል ሥልጣኑ ያላቸው ሲሆን ያለ ፍርድ ቤት ውሳኔ የአሠሪዎችን ንብረትም ቢሆን ለመውሰድ ይችላሉ።

በውጤታማ ማበረታቻ ያልተደገፈ አስገዳጅ ኮታ

- በዚህ ዓይነቱ ኮታ ስር የአካል ጉዳተኞችን የተወሰነ ኮታ እንዲቀጥሩ አሠሪዎች በሕግ ይገደዳሉ።
- ስለማይኖር ወይም ማበረታቻው ተፈጻሚ ስላልሆነ ይህ ግዴታ በውጤታማ ማበረታቻ የተደገፈ አይደለም።
- ምክንያቶች የሚያካትቱት፦
  - ለማበረታቻ ሕጋዊ ደንብ የለም፤
  - የኮታ ግዴታ ባልተሟላበት ሁኔታ ጉዳዮችን ላለማየት የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች ወስነዋል።

ታላቋ ብሪታኒያ - ምሳሌ

- ተፈጻሚነቱ በፍርድ ቤቶች አማካይነት እንዲሆን ታስቦ በ1944 ሦስት በመቶ ኮታ በሕግ ተመሠረተ።
- በ1993 ከ20 በመቶ በታች እንግሊዛውያን አሠሪዎች ኮታውን አሟሉ።
- ኮታው በጥብቅ ተፈጻሚ አልሆነም፣ ምክንያቱም፦
  - ከግዴታው ነፃ የመሆን ፈቃዶች ለአሠሪዎች ተሰጥተው ነበር፤
  - በሕግ ተላላፊ አሠሪዎች ላይ የቀረቡ ክሶች በጣም ጥቂት ነበሩ።
- ኮታው በ1996 ተወግዶአል።

ታይላንድ - ምሳሌ

- የታይላንድ የኮታ አሠራር በ1991 ተመሠረተ፡፡
  - ለግል አሠሪዎች፤
  - ለሕጉ አለመገዛት ቢኖር የቀረጥ ደንብ፡
- ምንም የማስፈጸሚያ አሠራር የሌለ ሲሆን ጫናው ውሱን ነበር፡፡
- በአዲሱ የ2007 ሕግ ስር፡-
  - ኮታው የመንግሥትና የግል አሠሪዎች አካል ጉዳተኞችን እንዲቀጥሩ ግዴታ ያካትታል፡፡
  - ለማይስማሙ አሠሪዎች አማራጮች ክፍት ናቸው፡፡
  - አማራጮች በማይወሰዱበት ሁኔታ መቀጫ ተከፋይ ይሆናል፡፡
  - የአንድ አሠሪ ለሕጉ ተገዢነት ለሕዝብ እንዲታወቅ ይደረጋል፡፡

አስገዳጅ ያልሆነ ኮታ

- ‹የሚደገፍ› የኮታ ሥርዓት – አሠሪዎች ይህን እንዲያከብሩ ይበረታታሉ።
- በኮታው መስማማት በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ ነው።
- አለመስማማት ቢኖር ምንም ማዕቀቦች የሉም።

የኔዘርላንድስ ተመክሮ

- በኔዘርላንድስ አስገዳጅ ያልሆነ የኮታ አሠራር በ1980ዎቹ አጋማሽ ነበር።
- ኮታው በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ መሳካት ያለበት በሦስትና በአምስት ከመቶ መከከል የተቀመጠ ዒላማ ነበር።
- ከ3 ዓመት በኋላ በመንግሥት የተደረገው ግምገማ ያገኘው መሻሻል አነስተኛ ነበር - ስለዚህ አሠራሩ ተወገደ።
- በ1990ዎቹ መጨረሻ የወጣ ሕግ ከ3 እስከ 7 በመቶ አስገዳጅ ኮታ የመጀመርን መቻል ያዝዛል፣ ግን ተፈጻሚ አልሆነም።

ኮታው በተግባር እንዲሠራ ማድረግ - መጤን ያለባቸው ጭብጦች

- የትኛዎቹ አካል ጉዳተኞች በኮታ አሠራር ዒላማ መሆን ይኖርባቸዋል?
- በኮታው ስር ለሥራ ስምሪት ብቁ የሆኑት እንዴት ይለያሉ?
- ወጥ ኮታ ወይስ የተለያየ የኮታ መጠን ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል?
- ተገቢው የኮታ መቶኛ ምንድን ነው?
- አነስተኛና መካከለኛ መጠን ያላቸው አሠሪዎች መካተት ይኖርባቸዋል?
- የመንግሥትና የግል አሠሪዎች መሸፈን ይርባቸዋል?
- ለአሠሪዎች ምን አማራጮች ክፍት መሆን ይኖርባቸዋል?

ሁሉን ወይም ጥቂቶቹን አካል ጉዳተኞች ዒላማ ማድረግ

- በዘዴው ዓላማ ላይ ይመረኮዛል፡፡
- ሁሉንም አካል ጉዳተኞች ዒላማ ማድረግ፡-
  - ዓላማው በአካል ጉዳት ጥቅሞች የሚኖሩትን ለመቀነስ ከሆነ አሠሪዎች ቀላል አካል ጉዳት ያለባቸውን ለመቅጠር ይመርጡ ይሆናል፡፡
- የሥራ ስምሪት በማግኘት ረገድ ታላላቅ ችግሮች የሚያጋጥሙአቸውን ዒላማ ማድረግ፡-
  - ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደረጃዎች ያሉባቸው ሰዎች በግል ብቃቶቻቸው ለሥራ መደቦች የመወዳደርና የማሸነፍ ያነሰ አጋጣሚ ይኖራቸው ይሆናል፡፡
  - የዚህን ቡድን የሥራ ስምሪት ዕድሎች ለማሳደግ በኮታ አማካይነት ዒላማ የተደረገ አዎንታዊ ተግባር እርምጃ ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡

ለኮታው ብቁ የሆኑትን መለየት

- ግለሰቡ ካለበት እክል ይልቅ በውሱን የመሥራት አቅሙ ዙሪያ የሚያተኩር የአካል ጉዳት ትርጓሜ መፍጠር፡፡
- እንዲህ ያሉት ሰዎች በአስተዳደራዊ መንገድ ተለይተው የሚታወቁበትን ዘዴ መፍጠር፡-
  - ለምሳሌ የምዝገባ አሠራር፡፡
- የሥራ ስምሪት ለማግኘትና ይዞ ለመቆየት ተያያዥ በሆኑ ተጨማሪ ጥቅሞች አሰጣጥ አማካይነት (እንደ መገለል፣ ባለመቻል ላይ ማተኮር፣ የህክምና ምርመራ ላሉ) ለማንኛውም ተስፋ አስቆራጭ ምዝገባ ማካካሻ መስጠት፡፡

አዘውትሮ ዒላማ የሆኑ የተወሰኑ ቡድኖች

- አንዳንድ ኮታዎች የተወሰኑ ቡድኖችን ዒላማ ያደርጋሉ፡-
  - በተለይ ጽኑ አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች፤
  - አካል ጉዳተኛ ከጦርነት ተመላሾች፤
  - የሥልጠናና የለማጅ ቦታዎችን የሚይዙ አካል ጉዳተኞች፤
  - ከፆታ፣ ዕድሜ፣ ሃይማኖት ወይም ፆታዊ ዝንባሌ ጋር ተዳብሎ በአካል ጉዳት ምክንያት ድርብርብ መድልዎ የሚያጋጥማቸው ሰዎች።
- በተወሰኑ ሰዎች የተሞሉ ቦታዎች ለኮታው ዓላማዎች ሲባል ከአንድ በላይ እንደ ሆኑ ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ።

ወጥ ኮታ ወይስ የተለያየ የኮታ መጠን?

- የተለያዩ የኮታ መጠኖች ሊያገለግሉ የሚችሉት፡-
  - አንዳንድ ክፍሎች ወይም ክልሎች ጽኑ አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች አመቺ የሆኑ በዛ ያሉ የሥራ መደቦች የሚሰጡ ከሆነ፤ ወይም
  - አንዳንድ ክፍሎች ወይም ክልሎች ጽኑ አካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች አመቺ የሆኑ ውሱን ቁጥር ያላቸውን የሥራ መደቦች ብቻ የሚሰጡ ከሆነ፡፡

የኮታ መቶኛዎችን መወሰን

- መረጃ የሚፈለግባቸው ነጥቦች፦-
  - ለሥራ ፈቃደኛና ዝግጁ የሆኑ አካል ጉዳተኞች ብዛት፤
  - ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ብዛት፤
  - ኩባኒያዎች በኤኮኖሚው ውስጥ ያላቸው መጠንና አጭር ታሪክ።
- የሥራ ፈላጊዎች ብዛት አንዴ ተለይቶ ከታወቀ የኮታ መጠን ተፈላጊ የሥራ መደቦችን ለመስጠት መታቀድ ይኖርበታል።

በኮታ የሚሸፈኑ አሠሪዎች

- ኮታዎች አዘውትረው ከተወሰነ መጠን በላይ የሥራ ኃይል ላላቸው አሠሪዎች ያገለግላሉ (ለምሳሌ ከ10 በላይ፣ ከ20 በላይ፣ ወይም ከ200 በላይ አሠሪዎች)፡፡
- የአነስተኛና መካከለኛ ኩባኒያዎች ከሽፋኑ መውጣት፡-
  - አዘውትሮ በኤኮኖሚያዊ ጭብጦች ላይ የተመሠረተ – አነስተኛ ኩባኒያዎች ማናቸውንም የሚከተሉ ተጨማሪ ወጪዎችን ለማጠቃለል ያቅታቸዋል፤
  - ግን በብዙ አገሮች አብዛኛዎቹ አሠሪዎች አነስተኛ ወይም መካከለኛ መጠን ያላቸው ናቸው፣ ስለዚህም እንዲወጡ ይደረጋሉ፤ እንዲሁም
  - አካል ጉዳተኞችን በማኅበራዊ ደረጃ ለማካተት አነስተኛ ኩባኒያዎች ሊሰጡ የሚችሉት ዕድል ይታጣል፡፡
- አነስተኛ አሠሪዎች በኤኮኖሚው ውስጥ ባላቸው አስፈላጊነት ላይ ተመሥርቶ ሚዛናዊ ውሳኔ ያስፈልጋል፡፡

ለአሠሪዎች ክፍት የሆኑ አማራጮች

- በብዙ አገሮች አሠሪዎች ሥራ ይሰጣሉ፣ ወይም ማካካሻ መጠን ይከፍላሉ።
- በፈረንሳይ ባሁኑ ጊዜ አሠሪዎች ግዴታቸውን በከፊል ሊሚያሚሉ በሚችሉበት ሁኔታ አማራጭ ምርጫዎች ተዘጋጅተውላቸዋል፤ ምርጫዎቹም፡-
  - ባለ መጠለያ ማምረቻዎች እንዲያመርቱ ወይም አገልግሎቶችን እንዲሰጡ በመዋዋል፤
  - የሥራ ላይ ሥልጠናዎችን በመስጠት፤ ወይም
  - አካል ጉዳተኛ ሠራተኞችን ለመመልመልና ለማሠልጠን እንዲሁም/ወይም በሥራ ቦታው ቴከኒካዊ ማስተካከያዎችን ለማድረግ የጋራ ዕቅዶችን በመቅረጽና ስምምነት በማድረግ ናቸው።